# መሪዎቻችን ታዘብናቸው

**ክፍል አንድ**

**ተፈሪ መኮንን**

**05-23-18**

ይህ መጣጥፍ በሐገራችን ሚዲያ ጉዳይ ያጠነጥናል፡፡ መጣጥፉ ለሚያነሳቸው ጉዳዮች ማዳወሪያ አድርጌ የያዝኩት፤ የተለያዩ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች ተሳታፊ የሆኑበት እና ባለፈው ወር አጋማሽ (ጥር 12/2010 ዓ.ም) የኢትዮጵያ የብሮድካስት ባለሥልጣን፤ ‹‹የሐገራችን ሚዲያ አዝማሚያዎች›› በሚል ርዕስ ባካሄደው ውይይት የተነሱ አንዳንድ ጉዳዮችን ነው፡፡ በዚሁ የውይይት መድረክ የብሮድካስት አገልግሎት ምህዳሩ ብቻ ሣይሆን፤ የሣይበር ምህዳሩም ትኩረት አግኝቷል፡፡ የሳይበሩን ነገር መነሻ አድርጌ የመንግስት ሚዲያዎችን እና የተቆጣጣሪውን የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን የተወሰኑ ችግሮች ለማየት እሞክራለሁ፡፡

## የሣይበሩ ምህዳር

የሣይበር ምህዳሩን ገና በውል አናውቀውም፡፡ አዲሱ የመገናኛ ቴክኖሎጂ ዕድገት የፈጠረው ይህ አዲስ ምህዳር፤ ለእኛ ቀርቶ የዳበረ የዴሞክራሲ ባህል ላላቸው እና የቴክኖሎጂው ባለቤት ለሆኑት ህዝቦችም ጭምር ግራ አጋቢ ሁዳድ ነው፡፡ ይህ ምህዳር ከፍተኛ አደጋ መጋረጡን እያየን ነው፡፡ ሁሉንም ወገን ‹‹ኧረ መላ በሉ›› እያሰኘ ነው፡፡

በዚህ የተነሳ ዓለም ምንነቱ በውል ተለይቶ በማይታወቅ እና ዕረፍት የሚነሳ ፍጥነት ባለው ‹‹የአብዮት ጎዳና›› እየተራመደች ነው፡፡ ይህ አብዮት ከዚህ ቀደም የምናውቀው የህትመት ቴክኖሎጂ በዓለም ላይ ከፈጠረው ሁለ-ገብ አብዮት ጋር ሲነጻጸር በተጽዕኖው እጅግ የላቀ ነው፡፡ የህትመት ቴክኖሎጂ መፈጠር የዓለምን መልክን እና ባህርይ ምን ያህል እንደ ቀየረው እናውቃለን፡፡ በህትመት ቴክኖሎጂ መፈጠር የተነሳ፤ ለብዙ ጊዜ የጥቂቶች ልዩ ሐብት ሆነው የቆዩት መጻህፍት ለብዙዎች የሚዳረሱበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህ አብዮት፤ ሰው ከሰው ጋር ያለውን ግንኙነት ብቻ ሳይሆን ሰው ከአምላኩ ጋር ያለውን ግንኙነት በእጅጉ ቀይሮታል፡፡

በርግጥ በወቅቱ በነበሩት የአውሮፓ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ይገኙ የነበሩት መጻህፍት በጣት የሚቆጠሩ ነበሩ፡፡ አንዳንዶች፤ በአውሮፓ ቤተ መጻሕፍት የነበሩት ሁለት መጻሕፍት ነበሩ ይላሉ -መጽሐፍ ቅዱስ እና የአርስጣጣሊስ ኢንሳይክሎፒዲያ፡፡ በስተቀር ሌላ መጽሐፍ አልነበረም፡፡ እዚህን መጻሕፍት ለማየት የሚችሉት ጥቂት ቀሳውስት እና መሳፍንት ነበሩ፡፡ የጥበብ ማዕድ የሆኑት መጻሕፍት የጥቂት መሳፍንት ወይም ቀሳውስት ሐብት ሆነው ለብዙ ዘመናት ቆይተዋል፡፡

ከህትመት ቴክኖሎጂ መፈጠር በኋላ፤ የታሪክ ምሁራን ‹‹ራስን የመግለጥ ዘመን›› (The Age of Expression) ሲሉ የሚጠሩት ዘመን መጣ፡፡ ይህ ዘመን ተራው ህዝብ ነገስታቱ እና ጳጳሱ ምን እንደሚያስቡ ወይም ምን እንደሚያደርጉ እስኪነግሯቸው ድረስ በዝምታ ቁጭ ብለው የሚጠብቁ ዜጎች መሆናቸው ያበቃበት አዲስ ዘመን ነበር፡፡ ተራው ህዝብ ተደራጊ ብቻ ሳይሆን አድራጊ መሆን የጀመረበት ዘመን ነበር፡፡ ዜጎች ከህይወት መድረክ ወጥተው ተዋናይ ሆኑ፡፡ ብዙዎች የግል አስተያየት እና ሐሳባቸውን ለመግለጽ የሚፈልጉ ሰዎች ሆኑ፡፡ እንደ ፍሎሬንሱ የታሪክ ጸሐፊ ኒኮሎ ማክያቬሊ በመንግስት አመራር ጥበብ ጉዳይ የሚሉት ሐሳብ ካላቸው፤ መጽሐፍ ጽፈው፤ ‹‹ጥሩ መሪ እንዲህ ያለ ነው›› እያሉ፤ የግል ሐሳባቸውን መግለጽ የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ታዲያ ‹‹ራስን የመግለጥ ዘመን›› መጻህፍት በመደጎስ የተወሰነ አልነበረም፡፡ ሐሳቡን በቀለም መግለጽ የሚሻ በስዕል፣ በሚዳሰስ ቁስ ሊገለጽ የሚችል ሐሳብ አለኝ የሚል -በቅርጻ ቅርጽ ወዘተ ሐሳቡን ይገልጽ ጀመረ፡፡ ሙዚቃ እና ሥነ ህንጻም ራሳቸውን መግለጽ ለሚፈልጉ ሰዎች ዘይቤ (መባያ) ሆኑ፡፡

በሐገረ ጀርመን ውስጥ ሜይንዝ (Mainz) በተባለች ከተማ ይኖር የነበረው ሰው ያመጣው ነገር የዓለምን ሁኔታ ቀይሯል፡፡ ጆሐን ዙም ጋንሴፍለሽ (Johann zum Gansefleisch) በሚል የሚጠራው እና በብዙዎች ዘንድ ጆሐን ጉተንበርግ በሚል ስም የሚታቀው ሰው፤ መጽሐፍን የማባዛት አዲስ ጥበብ መፍጠሩ አብዮት አስነሳ፡፡ በመጀመሪያ በመላ ጣሊያን (ብዙም ሳይቆይ በመላ አውሮፓ) ‹‹በሰው ልጆች የዕውቀት፣ የውበት እና የጥበብ መጋዘን ውስጥ አንድ የምጨምረው ነገር አለ›› ብለው የሚያስቡ ሰዎች በረከቱ፡፡ ጉተንበርግ ከፈጠረው የህትመት ቴክኖሎጂ ጋር በተያያዘ የፍትሐ-ብሔር ክስ ተመስርቶበት፤ በክርክሩ ገንዘቡን ጨርሶ በድህነት ተቆራምዶ ለሞት በቃ፡፡ የእርሱ እኩያ ሆኖ በዛሬው ዘመን የተነሳው ማይክል ዙከንበርግ ግን በሐብት እየተንበሸበሸ ነው፡፡

ጆሐን ጉተንበርግ፤ በሊድ የተቀረፁ ፊደላትን በመጠቀም ቃላት አቀናብሮ መጽሐፍ የማተም ጥበብን ለዓለም ሲያበረክት፤ በላቲን፣ በእብራይስጥ እና በግሪክ ቋንቋዎች የተለያዩ መጻህፍት እየታተሙ ይወጡ ጀመር፡፡ ዓለምም ‹‹አንዳች የምለው ነገር አለኝ›› የሚሉ ሰዎች የሚያነሱትን ሐሳብ ለመስማት በእጅጉ የምትጓጓ ሆነች፡፡

መማር ወይም ማንበብ የጥቂት ዕድለኞች ሰዎች ፀጋ ሆኖ የቆየበት ዘመን አከተመ፡፡ ድንቁርናን ታቅፈው የሚኖሩ ሰዎች የመጨረሻ ሰበብ አድርገው የሚያነሱት (‹‹መጽሐፍ የት ይገኛል ብላችሁ ነው››) የሚል መከላከያ ከዓለም ተወገደ፡፡ ለብዙሃኑ ህዝብ የሚመጥን ይዘት ያላቸው እና በርካሽ ዋጋ ሊገዙ የሚችሉ መጻሕፍት መታተም ጀመሩ፡፡ የጥንታዊ ፈላስፎች የእነ አርስጣጣሊስ፣ አፍላጦን፤ የጥንታዊ ደራስን የእነ ቨርጅል፣ የሆሬስ እና ፐሊኒ ሥራዎችን በትንሽ ሣንቲም ገዝቶ ማንበብ የሚቻልበት አዲስ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ የህትመት ቴክኖሎጂ ሁሉም ሰዎች ነጻ እና እኩል መሆናቸውን አረጋገጠ፡፡ ዓለም በህትመት ጥበብ መፈጠር ምን ያህል እንደ ተቀየረች ለመረዳት ብዙ የታሪክ ሁነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሆኖም ነገር እንዳይረዝም በደፈናው ‹‹ዓለምን ተቀየረች›› ብዬ ልለፈው፡፡

አሁን ደግሞ አዲሱ የመረጃ ቴክኖሎጂ (ሣተላይት፣ ሞባይል፣ ኮምፒዩተር፣ ኢንተርኔት ወዘተ) ‹‹በሳይንሳዊ ልቦለድ ውስጥ የምንኖር እንዲመስለን አድርጓል፡፡›› የሰው ሰራሽ አዕምሮ ቴክኖሎጂ (Artificial Intelligence) የዓለምን መዳረሻ አጓጊ አድርጎታል፡፡ አንድምታው ገና ያልታወቀ አብዮት ይዞብን መጥቷል፡፡

በአጠቃላይ አዲሱ የመረጃ ቴክኖሎጂ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት (በተለይም ባለፉት አምስት ዓመታት) ለወሬ በሚያስቸግር ሁኔታ የሰውን ህይወት በጥልቀት እና በፍጥነት እየቀየረው ይገኛል፡፡ ከዚህ ቴክኖሎጂ ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩትን አዳዲስ የአገልግሎት ዓይነቶች ለመገመት አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ መስኩ ጨርሶ ከኔ ክበብ የወጣ በመሆኑ፤ በአጭር አማርኛ ‹‹ዓለም የሚሳራትን አሳጥቷታል›› ብዬ ባልፈው ይሻለኛል፡፡ አንዱን የመረጃ ቴክኖሎጂ ትሩፋት አጣጥመን ወይም በወጉ ተረድተን ሳንጨርስ ሌላው ይመጣል፡፡ ‹‹መተግበሪያው›› በእናት በእናቱ ይመጣል፡፡ የለውጡ ፍጥነት ትንፋሽ የሚያሳጥር ነው፡፡ ቀድሞ ከምናቀው ዓለም ፍፁም የተለየ እና ገና ባህርይውን ጠንቅቀን ለማወቅ ያልቻልነው አዲስ ሰው ሰራሽ ምህዳር ተፈጥሯል፡፡ ይህ ቴክኖሎጂ ‹‹የት ያደርሰን ይሆን?›› የሚያሰኝ ሥጋት ፈጥሯል፡፡

ለወትሮው የምናውቃቸው የብስ፣ ባህር፣ አየር የሚባሉ የተፈጥሮ ምህዳሮችን ነበር፡፡ አሁን የመጣው ሰው ሰራሽ ምህዳር ‹‹ሳይበር›› ይሉታል፡፡ ስሙም አማርኛ ይመስላል፡፡ ባለፉት ሁለት አስርት በፍጥነት እያደገ የመጣው፤ ይህ አዲስ ምህዳር ከዚህ ቀደም ከኖሩ ሰዎች ተመክሮ እና የህይወት ልምድ የምናገኝበት ምህዳር አይደለም፡፡ ይህ ቴክኖሎጂ በአንድ ትውልድ ዕድሜ ተወልዶ፤ ለመረዳት በሚያስቸግር ፍጥነት እያደገ የሚገኝ ቴክኖሎጂ በመሆኑ፤ በትሩፋቱ እየተጠቀመ እና በክፋቱ እየጎዳ ያለው፤ የቴክኖሎጂ ፈጣሪው ትውልድ ነው፡፡

በዚህ ሰው ሰራሽ ምህዳር ያለውን አደጋ እና ፀጋ እየቀመስን በምህዳሩ የምንንከራተተው ሁላችንም ነን፡፡ እንደ ኮሎምበስ ወይም ማጂላን ያሉ በርካታ አሳሾች መከራ አይተው እና ተንገላተው መረጃ ከሰበሰቡ በኋላ የገባንበት ምህዳር አይደለም፡፡ ይህ ትውልድ ድንገት ሳያስበው፤ ጊዜን እና ቦታን አኮማትሮ፤ ዓለምን በመዳፍ ውስጥ ማስገባት የሚችል ቴክኖሎጂ ባለቤት ሆኗል፡፡ እንዲህ ያለውን ክስተት ለመግለጽ ‹‹ዓለም አንድ መንደር ሆነች›› እንላለን፡፡ በዚህ ቴክኖሎጂ የተነሳ፤ በአሜሪካ እና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ርቀት አንድ የኮምፒዩተር ቁልፍ ለመጫን በሚወስደው ጊዜ የሚመጠን ሆኗል፡፡ ‹‹ሳይበር›› የሚባለው ምህዳር የምንኖርባትን መሬት ከአንድ ጨሌ ያነሰች አድርገን እንድንቆጥራት የሚያደርግ ሰፊ ዓለም ነው፡፡ አሁን 5-ጂ ከሚባለው እጅግ እጅግ ፈጣን የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ደርሰናል፡፡ ቴክኖሎጂው፤ በትምህርት፣ በህክምና፣ በንግድ፣ በማህበራዊ መስተጋብር ወዘተ አስደናቂ ሁኔታ እየፈጠረ ነው፡፡ በአጭሩ ‹‹በአንድ ሳይንሳዊ ልብወለድ የምንገኝ ገጸ ባህርያት አድርጎናል፡፡›› ይህ ሁኔታ እንኳን ቴክኖሎጂውን በመቅዳት ለመጠቀም ለምንሞክረው ለእኛ፤ ለባለቤቶቹም ዓመሉ ያልታወቀ አውሬ ሆኖባቸዋል፡፡

እንግዲህ አሁን የምንኖርባት ኢትዮጵያ በዚሁ ቴክኖሎጂ ፀጋ የምትጠቀም እና ቴክኖሎጂው ባመጣው አደጋ የምትንገላታ ነች፡፡ ከአዳዲሶቹ ቴክኖሎጂዎች ጋር ተያይዞ የሚመጣውን ለውጥ የሚተነብዩ የዘርፉ ባለሙያዎች፤ አዳዲሶቹ ቴክኖሎጂዎች ብዙ ዓመታት ሳይወስዱ በህይወታችን ወይም በአሰራራችን ላይ ለውጥ እንደሚያመጡ ይነግሩናል፡፡ ቴክኖሎጂዎቹ በሦስት እና በአራት ዓመታት ውስጥ አሁን የምንገኝበትን ሁኔታ ሙሉ በሙሉ እንደሚቀይሩት ይነግሩናል፡፡ በዚህ ቴክኖሎጂ የተነሳ የቋንቋ አጥር ይረመሳል፡፡ የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ ሁለት ሰዎች በዛው በሚናገሩበት ቅጽበት ሐሳባቸው እየተተረጎመ መነጋገር የሚችሉበት ከሞባይል ጋር የተያያዘ ቴክኖሎጂ ተፈጥሯል፡፡ ይህን ጽሑፍ በምጽፍበት ጊዜ ይህ ቴክኖሎጂ በሐገረ - ሆላንድ ሙከራ እየተደረገበት አይቻለሁ፡፡ አንድ የሲ.ኤን.ኤን ጋዜጠኛ በጎዳና ወጥቶ 80 ቋንቋዎችን ለመተርጎም የሚችለውን መሣሪያ በመጠቀም ለሰዎች ቃለመጠይቅ ሲያደርግ ተመልክቻለሁ፡፡ ‹‹ጉድ በል ጎንደር›› ማለት አሁን ነው፡፡

ከዚህ ቀደም በመገናኛ ብዙሃን ቴክኖሎጂ ረገድ ይታዩ የነበሩት ለውጦች እርጋታ ነበራቸው፡፡ አሁን እርጋታ የሚባል ነገር የለም፡፡ ከአንዱ አስደናቂ ቴክኖሎጂ ይበልጥ አስደናቂ ወደ ሆነ ሌላ የቴክኖሎጂ ውጤት በቀናት፣ በሣምንት፣ በወራት ጊዜ መሸጋገር የተመደ ሆኗል፡፡ በስልክ፣ በሬዲዮ እና በቴሌቭዥን መካከል የዓመታት ፋታ እያገኘን ስንሸጋገር ቆይተን ነበር፡፡ የአሁኑ ለውጥ በቅጽበት ዕድሜ የሚመጠን ነው፡፡